በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ህዳር 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አመሰራረት 1

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር 2

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዓላማ 2

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባር 2

በኦዲቱ የተመረጡ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አደረጃጀትና የሰው ኃይል 3

አደረጃጀት 3

በኦዲቱ የተመረጡ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሰው ኃይል 4

የፋይናንስ ምንጭ 5

የተመላላሽ ታካሚዎች ፍሰት የሥራ ሂደት መግለጫ 6

የኦዲቱ ዓላማ 7

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 7

ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ 8

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ 8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 8

ክፍል ሁለት 9

የኦዲት ግኝቶች 9

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የህሙማን አላላክና አቀባበል (ሪፈራል) ስርዓትን በተመለከተ፤ 9

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎች አቀባበልና

የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባን
በተመለከተ፤..
...............10

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በምልክቶችና በቀለም
መለየታቸውን በተመለከተ 12

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚከታተል የሆስፒታል 12

ቦርድ በሁሉም ሆስፒታሎች መቋቋሙን በተመለከተ፤ 12

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣ 14

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ግብዓቶችን እና መመሪያዎችን በተመለከተ፤ 15

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ መሆናቸውን በተመለከተ፤ 16

በፌደራል ሪፈራል ሆስፒታል የሚታከሙ ተመላላሽ ታካሚዎች በስፔሻሊስት ሀኪም የሚታዩ መሆኑን በተመለከተ፤ 18

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና እና የምርመራ መሳሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ፤ 19

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ በቂ የሆነ የታካሚዎች ማረፊያ ቦታ፣ መፀዳጃ ቤት፣ 24 ሰዓት የውሃና የመብራት አገልግሎት እና የኢንፌክሽን መከላከል ክፍል መኖሩን በተመለከተ፤ 22

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የመድኃኒት አቅርቦት እና አጠቃቀምን የሚከታተል የመድሃኒት እና ቴራፔቲክ ኮሚቴ (Drug and Therapeutic Committee) መቋቋሙን በተመለከተ፤ 23

ክፍል ሶስት 25

መደምደሚያ 25

ክፍል አራት 27

የማሻሻያ ሃሳቦች 27

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የታካሚዎችን አቀባበል እና የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና የታካሚዎችን ፍላጎት የሚያሟላ እንዲሆን ለማስቻል፤ 27

አባሪ .... i--iv

ክፍል አንድ

መግቢያ

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አመሰራረት

1. በኢትዮጵያ የጤናው ዘርፍ በሦስት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ የአደረጃጀት እርከኖች ተደራጅቷል፡፡ የመጀመሪያው እርከን መሰረታዊ ሆስፒታሎችን የሚያጠቃልል ሲሆን እነሱም ወረዳ አቀፍ መሰረታዊ ሆስፒታል (ከ60,000- 100,000 ህዝብ የሚሸፍን)፣ ጤና ጣቢያ (ከ15,000- 25,000 ህዝብ የሚሸፍን) እና ጤና ኬላ (ከ3,000- 5,000 ህዝብ የሚሸፍን) ናቸው፡፡ ሁለተኛው የእርከን ደረጃ አጠቃላይ ሆስፒታልን የሚይዝ ሲሆን ከ 1 ሚሊዮን እስከ 1.5 ሚሊዮን ለሚሆን ህዝብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ሦስተኛው የአደረጃጀት እርከን የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚይዝ ሲሆን ከ3.5 ሚሊዮን እስከ 5 ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ ይሸፍናል፡፡
2. የፌደራል ሆስፒታሎች ለኢትዮጵያ የጤና አጠባበቅ ስርዓት ከሚያበረክቱት ውስጥ ለህሙማን ከፍተኛ የህክምና አገልግሎት መስጠት፣ የኢትዮጵያ ሃኪሞች የሚማሩበት፣ ልዩ ልዩ ጤና እና ጤና ነክ የሆኑ ምርምርና ጥናት የሚደረግበት፣ ለጤና ባለሙያዎች የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን የሚሰጡበት ተቋማት ናቸው፡፡
3. በኢትዮጵያ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ከ200 በላይ ሆስፒታሎች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል አስራ አንዱ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ናቸው፡፡ ከአስራ አንዱ አራቱ ማለትም ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ፣ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና አለርት ማዕከል ተጠሪነታቸው ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሲሆን የተቀሩት ሰባቱ ማለትም ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ሃረማያ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና አዳማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል (አሰላ) ደግሞ የዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ሆነው በትምህርት ሚኒስቴር ስር ይገኛሉ፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዓላማ

4. የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዋነኛ ዓላማ የህብረተሰቡን የጤና ሁኔታ ማሻሻል፤ በድንገተኛ፣ በተመላላሽ እና ተኝተው በሚታከሙ ህሙማን ህክምና ክፍሎች ለታካሚዎች ቀልጣፋና ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት መስጠት፤ በህክምና ሙያ በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም ለመካከለኛ ጤና ባለሙያዎች የድግሪ፣ ለመጀመሪያ ደረጃ የህክምና ዶክትሬት ድግሪ እና ለተለያዩ የከፍተኛ እና የድህረ ምረቃ ስፔሻሊስቶች ስልጠና መስጠት፤ እንዲሁም በጤናው ዘርፍ የምርምር ትኩረት መስኮችን በመለየት በዋና ዋና የጤና ችግሮችና የጤና አገልግሎት ሥርዓቶች ዙሪያ ተግባራዊ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ (ለማስተማሪያ ሆስፒታሎች) ናቸው፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባር

5. ከፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የህብረተሰቡን የጤና ሁኔታ ማሻሻል፤ በድንገተኛ፣ በተመላላሽ እና ተኝተው በሚታከሙ ህሙማን ክፍሎች ለታካሚዎች ቀልጣፋና ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት የመስጠት፤
- የጤና ችግሮችን ለመፍታት፣ በጤናው መስክ በቂና አግባብ ያለው የሰው ኃይልን ለማፍራት በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠኑ በተለይም በህብረተሰቡ ፍላጎት ያተኮሩና የህብረተሰቡን ፍላጎት የሚያሟሉ፣ በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፁ እና ለተግባር የተዘጋጁ ባለሙያዎችን በዓይነት፣ በጥራትና በብቃት የማፍራት፤
- በአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር ከሚገኙ የጤና ተቋማት እና ሌሎች ለጋሽ ደርጅቶች ጋር የጠበቀ የሥራ ትብብርን በመፍጠር በስልጠና፣ በምርምር እና በህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል፤
- በምርምር መስክ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የህብረተሰቡን የጤና ችግሮች መፍትሄ የመፈለግና በህክምና ዘርፍ እድገትን ማምጣት፤

በኦዲቱ የተመረጡ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አደረጃጀትና የሰው ኃይል አደረጃጀት

6. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በቦርድ የሚተዳደር ሲሆን ቦርዱ ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፡፡ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ሆስፒታሉ እና ኮሌጁ በአንድ ላይ የሚተዳደሩ ሲሆን በአንድ ዋና ፕሮቮስት እና ሶስት ምክትል ፕሮቮስቶች (የሜዲካል ሰርቪስ ም/ፕሮቮስት፣የአካዳሚክ ፕሮግራምና ምርምር ም/ፕሮቮስት እና የአስተዳደርና የልማት ም/ፕሮቮስት) ይመራል፡፡ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለሜዲካል ሰርቪስ ም/ፕሮቮስት የሆኑ የተመላላሽ ህክምና ዳይሬክቶሬት፣ የተኝቶ ህክምና ዳይሬክቶሬት እና የድንገተኛ ህክምና ዳይሬክቶሬትን ጨምሮ 13 ዳይሬክቶሬቶች በኮሌጁ ይገኛሉ፡፡

7. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስር የሚተዳደር ሲሆን ተጠሪነቱም ለኮሌጁ ነው፡፡ ሆስፒታሉ በአንድ ዋና ስራ አስፈፃሚ (Chief Executive Officer (CEO))፣ በአንድ ሜዲካል ዳይሬክተር እና በአንድ ዋና አስተዳዳሪ ይመራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪነታቸው ለዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑ የተመላላሽ ህክምና ክፍል፣ የተኝቶ ህክምና ክፍል እና የድንገተኛ ህክምና ክፍል፣ እንዲሁም ሌሎች ክፍሎች (የፋርማሲ ክፍል፣ የላቦራቶሪ ክፍል፣ የአካባቢ ደህንነት ጤና አጠባበቅ ክፍል፣ የፋይናንስ መምሪያ ወዘተ) ይገኛሉ፡፡

8. የጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በጅማ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስር የሚተዳደር ሲሆን ተጠሪነቱም ለኮሌጁ ነው፡፡ ሆስፒታሉ ተጠሪነቱ ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን በሆነ አንድ ክሊኒካል ዳይሬክተር እና በክሊኒካል ዳይሬክተር ስር በሚገኙ ሁለት ምክትል አስተዳዳሪዎች ይመራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ነርሲንግ ዳይሬክተር፣ የተመላላሽ ህክምና ክፍል፣ የተኝቶ ህክምና ክፍል እና የድንገተኛ ህክምና ክፍል፣ የውስጥ ደዌ ክፍል፣ የህጻናት ህክምና ክፍል፣ የጽንስና ማህፀን ክፍል፣ የፋርማሲ ክፍል፣ የላቦራቶሪ ክፍል የሚገኙ ሲሆን ተጠሪነታቸውም ለክሊኒካል ዳይሬክተሩ ነው፡፡

9. የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በጎንደር ዩኒቨርስቲ ስር እንደ አንድ የስራ ሂደት የተዋቀረ ሲሆን የሚመራውም በሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚ (CEO) ነው፡፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ቦርድ ሲሆን ቦርዱ ደግሞ ተጠሪነቱ ለጎንደር ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪነታቸው ለዋና ስራ አስፈፃሚ

የሆኑ የተመላላሽ ህክምና ክፍል፣ የተኝቶ ህክምና ክፍል እና የድንገተኛ ህክምና ክፍል፣ እንዲሁም ሌሎች ክፍሎች (የፋርማሲ ክፍል፣ የዲያግኖስቲክ ክፍል፣ የግዥና ፋይናንስ ክፍል፣ ወዘተ) ይገኛሉ፡፡

በኦዲቱ የተመረጡ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሰው ኃይል

10. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በሰኔ ወር 2004 መጨረሻ 304 ሀኪም፣ 632 የጤና ባለሙያዎች፣ 712 የአስተዳደር ሰራተኞች፣ 86 የኮንትራት ቅጥር ጤና ባለሙያዎች እና 148 የኮንትራት ቅጥር አስተዳደር ሠራተኞች አሉት፡፡

11. የጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በሰኔ ወር 2004 መጨረሻ 53 ሀኪም፣ 256 የጤና ባለሙያዎች፣ 177 የአስተዳደር ሰራተኞች፣ 13 የኮንትራት ቅጥር አስተዳደር ሠራተኞች፣ እና 277 ጊዜያዊ/ የቀን አስተዳደር ሠራተኞች አሉት፡፡

12. የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በሰኔ ወር 2004 መጨረሻ 112 ሀኪም፣ 414 የጤና ባለሙያዎች፣ 673 የአስተዳደር ሰራተኞች፣ 116 የኮንትራት ቅጥር አስተዳደር ሠራተኞች አሉት፡፡

13. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በሰኔ ወር 2004 መጨረሻ 135 ሀኪም፣ 467 የጤና ባለሙያዎች እና 611 የአስተዳደር ሰራተኞች አሉት፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

14.በኦዲቱ የታዩት ሆስፒታሎች በ2002፣ በ2003፣ እና በ2004 የተመደበላቸው እና ጥቅም ላይ ያዋሉት በጀት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የሆስፒታሉ ስም	የተመደበ በጀት (በብር)				የተጠቀመው በጀት (በብር)			
		2002	2003	2004	ድምር	2002	2003	2004	ድምር
1.	የቅዱስ ጳውሎስ ሆ/ሚ/ሜ/ኮ	57,725,200	97,100,500	128,541,058.8	283,366,758.86	47,192,505.98	93,477,767.12	126,767,070.23	267,437,343.33
2.	የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል	55,407,291.16	67,148,598.6	105,184,435.6	227,740,325.36	52,454,349.02	61,186,712.60	94,601,050.2	208,242,111.82
3.	የጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል	24,067,700	29,184,468.84	32,001,075	85,253,243.84	24,077,581.49	28,452,468.84	30,871,570.95	83,401,621.28

ማስገንዘቢያ፡- የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል የሚመለከተው መረጃ ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የተመላላሽ ታካሚዎች ፍሰት የሥራ ሂደት መግለጫ

15. የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በተመላላሽ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በመሆኑ የሥራ ሂደት መግለጫው የተመላላሽ ህሙማንን ብቻ የሚመለከት ሆኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስራ ሂደት መግለጫው በኦዲት የተመረጡ አራቱም ሆስፒታሎች የሚጠቀሙበት ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

16. ተገልጋዩ ወይም ታካሚው በጥበቃ ሠራተኛ ሳይጠየቅ የሚፍልገውን አገልግሎት ለማግኘት በቀጥታ ወደ ሆስፒታሉ ይገባል፡፡ ከዚያም የሪፌራል ወረቀት በማየት የታካሚውን ሁኔታና የሚሄድበትን ኬዝ ቲም በመለየት ምዝገባና ለህክምና አገልግሎት የሚያስፈልግ ክፍያ (cash deposit) መቀበል፡፡ ቀጥሎም ወደሚመለከተው የህክምና ኬዝ ቲም መላክ፤ ካርዱ በራነር (በተላላኪ) ወደኬዝ ቲም ይላካል፤ በስልክ ሴንትራል ትራያጅ ቀጠሮ ያስያዙ ገንዘብ ካስያዙ በኋላ ወደሚመለከተው የህክምና ኬዝ ቲም ይላካሉ፤ ምርመራ ያካሂዳል፣ አስፈላጊ ዲያግኖስቲክ ምርመራዎችን ያዛል፤ ታካሚው ወደ ማዕከላዊ ናሙና መሰብሰቢያ ይሄዳል፣ ናሙና ይሰጣል/ ታካሚው ወደ ሌሎች ዲያግኖስቲክ ምርመራዎች በራነር (በተላላኪዎች) እገዛ ይላካል፤ ውጤት ኮምፒውተራይዝድ በሆኑ ላቦራቶሪዎች በIT እና በራነር ይመለሳል፤ ውጤቱ እንደደረሰ በባለሙያ ታይቶ ውሳኔ ይሰጣል፤ ታካሚው አስፈላጊ የሆኑ እና በክፍሉ መሰራት የሚችሉ መለስተኛ ፕሮሲጀሮች በታከመበት የህክምና ክፍል ያገኛል፤ ታካሚው የሚፈልገውን የህክምና ማስረጃ በታከመበት ኬዝ ቲም አግኝቶ ይሄዳል፤

17. የህክምና ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ በአስቸኳይ ተኝተው መታከም የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በአድሚሽን ኬዝ ቲም በኩል እንዲተኙ ይደረጋል፣ በቀጠሮ ለሚተኙ ታካሚዎች በአድሚሽን ኬዝ ቲም የአልጋ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው ይሄዳሉ፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሰብ ስፔሻሊቲ ኬዝ ቲም/ ሌላ ጀነራል ስፔሻሊስት ኬዝ ቲም በራነር (በተላላኪ) አማካይነት ተልከው የዚያኑ ቀን ይታያሉ፤ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ቀጠሮ ይዘው ወደ ቤት ይሄዳሉ፤ ህክምናቸውን የጨረሱ

መድሃኒት ማዘዣ ይዘው ይሄዳሉ፤ በሆስፒታሉ የሌለ አገልግሎት ከሆነ በላይዘን ኦፊሰሩ በኩል ለሚመለከተው ተቋም ግንኙነት በማድረግ ይላካል፡፡ የፋርማሲው ኬዝ ቲም ለታካሚው የታዘዘውን መድሃኒት ከአስፈላጊው መረጃ ጋር ይሰጠዋል፣ አስፈላጊ ሲሆን ክፍያ ይቀበላሉ፡፡ ስዕላዊ የተመላላሽ ታካሚዎች ፍሰት የሥራ ሂደት መግለጫ በሪፖርቱ በአባሪ-1 ተያይዟል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

18. የኦዲቱ ዓላማ በኦዲቱ የተመረጡት የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች (ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር) ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

19. ኦዲቱ የሸፈነው በሦስት የበጀት ዓመታትን ማለትም በ2002፣ በ2003 እና በ2004 ለተመላላሽ ታካሚዎች የተሰጠውን የህክምና አገልግሎት ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በተመረጡት አራቱ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች (ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል) የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ ቃለ መጠይቆችን እና የሰርቬይ መጠይቆችን በማቅረብ እና የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡

20. በዚህም መሰረት በአራቱም ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ለዋና ስራ አስፈፃሚ፣ ለሜዲካል ዳይሬክተር፣ ለምክትል አስተዳዳሪዎች፣ ለዩኒቨርስቲ ዲኖች፣ ለነርሲንግ፣ ለላቦራቶሪ፣ ለፋርማሲ፣ ለካርድ ክፍል ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም ለተመላላሽ ታካሚዎች እና ለባለድርሻ አካላት የሰርቬይ መጠይቆች በመላክ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

ለኦዲት የተመረጠው የኦዲቱ አካባቢ

21.በተመረጡት የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም የአገልግሎት መስጫ የህክምና መሳሪያዎች በቂ፣ ዘመናዊ እና የታካሚዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ (ታካሚዎች በሀኪሞች የሚታዘዙ ምርመራዎችን ከሆስፒታሉ እንዲያገኙ የሚያስችሉ) መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ

22. ከላይ በተለየው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡

እነሱም፡-

I. የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎች አቀባበል እና የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤

II. በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለህሙማን መርጃ የሚውሉ የህክምና መሳሪያዎች በቂ፣ ዘመናዊ እና የታካሚዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ (ታካሚዎች በሀኪሞች የሚታዘዙ ምርመራዎችን ከሆስፒታሉ እንዲያገኙ የሚያስችሉ) መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

23. ከላይ የተለዩትን የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 21 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ ሆስፒታሎች የማሻሻያ ትግበራ መመሪያ (Ethiopian Hospital Reform Implementation Guideline) ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አዋጅ እና መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሰነድ፣ የፌዴራል ሆስፒታሎች ደንብ፣ በኦዲት የተመረጡ ሆስፒታሎች መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሰነድ እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ-2 ተያይዘዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የህሙማን አላላክና አቀባበል (ሪፈራል) ስርዓትን በተመለከተ፤

24. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ሊገለገሉበት የሚገባ የተጠናከረ አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል /ሪፈራል/ ስርዓት ሊዘረጋ እና ስርዓቱም በአገሪቷ ያሉ ሆስፒታሎች ተቀናጅተውና ተናበው እንዲሰሩ ሊያስችል፣ ወጥ የሆነ የሪፈራል መመሪያ ሊያዘጋጅና በመመሪያው ላይ ግንዛቤ ሊፈጥር እንዲሁም ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ሊያወጣ ይገባል፡፡

25. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 475/1994 ንዑስ ክፍል 3(10) የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የማቋቋምና የማስተዳደር ስልጣን እንዲሁም መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይሁን እንጅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘረጋ አገር አቀፍ የሪፈራል ስርአት አለመኖር ይህም የሪፈራል ስርዓቱ የሚያካትታቸው ጉዳዮች ማለትም የሪፈራል ሆስፒታሎች የእርስ በርስ ትስስር፣ በሆስፒታሎች ውስጥ እና በሆስፒታሎች መካከል ተናቦ መስራት (inter and intra hospital communication) አለመቻሉ፣ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፣ አገር አቀፍ የሪፈራል መመሪያ አለመዘጋጀቱ እንዲሁም ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

26. በኦዲቱ ወቅት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መ/ቤት ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ በሰጡት መልስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሪፈራል ስርዓቱን ለማጠናከር መመሪያ አዘጋጅቶ እንዳሰራጨ ቢገልፁም በኦዲቱ በታዩት ሆስፒታሎች መመሪያውም ሆነ ስርዓቱ አለመኖሩ እንዲሁም የተዘጋጀ የህክምና ሥነ-ምግባር መመሪያ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

27. ከዚህ በተጨማሪ ለጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ለጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ኃላፊዎች በቀረበ መጠይቅ አገር አቀፍ የሪፈራል ስርዓትና

ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት ታካሚዎችን ካለ ሪፈር ወረቀት የሚቀበሉ በመሆኑ የታካሚዎችን ፍሰት ለመቆጣጠር መቸገራቸውን እና የታካሚዎች መጨናነቅ (congestion) መኖሩን ገልፀዋል፡፡

28. በተመሳሳይ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አገር አቀፍ የሪፈራል ስርዓት ባለመኖሩ እና ከዝቅተኛና መካከለኛ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር (networking) ባለመኖሩ የታካሚዎች አቀባበል ላይ ከፍተኛ ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ይህም በዝቅተኛ ሆስፒታሎች መታከም የሚችሉ ታካሚዎች ወደ ሪፈራል ሆስፒታሎቹ የሚመጡ በመሆኑ የሆስፒታሎቹ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና የተገልጋዩን ፍላጎት የሚያሟላ እንዳይሆን ማድረጉን ገልፀዋል፡፡

29.የሪፈራል መመሪያና ስርዓት ባለመኖሩ የታካሚዎችን ፍሰት መቆጣጠር እንዳይቻል እንዲሁም ቀልጣፋና ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት እንዳይኖር አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያው ባለመውጣቱ ሀኪሞች በሙያቸው ዙሪያ ያለውን የህግ ማዕቀፍ እንዳያውቁ እንዲሁም ታካሚዎች ስለሚያገኙት የህግ ከለላ ማወቅ እንዳይችሉ አድርጓል፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎች አቀባበልና የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባን በተመለከተ፤

30.ተመላላሽ ታካሚዎች በማንኛውም የስራ ስዓት ሊስተናገዱ፣ በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ዕቅድ መሰረት ታካሚዎች ሆስፒታል በደረሱ በ2 ስዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ሊያገኙ እንዲሁም የሆስፒታሉ ሀኪሞች ለሚያደርጉት የጠዋት ስብሰባ የመሰብሰቢያ ስዓት የጊዜ ገደብ ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡

31.የጥቁር አንበሣ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ታካሚዎችን የሚቀበሉት ጠዋት ብቻ መሆኑን፤ በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት እቅድ መሰረት ሁሉም ታካሚዎች በ2 ሰዓት ውስጥ አገልግሎት የማያገኙ መሆናቸውን እና በአራቱም ኦዲቱ በተከናወነባቸው የሪፈራል

ሆስፒታሎች የዶክተሮች የጠዋት ስብሰባ የሠዓት ገደብ የሌለ መሆኑ በተጨማሪም ከስብሰባ በኋላ በሻይ እረፍት ምክንያት ታካሚዎች ከ2 ሰዓት በላይ ዶክተሮችን የሚጠብቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

32. ይህንን በተመለከተ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሆስፒታሎቹ በቆየ የልምድ አሠራር ምክንያት ተመላላሽ ታካሚዎችን ጠዋት ብቻ የሚቀበሉ መሆኑን ይህም ለታካሚዎች አመቺ ካለመሆኑ በላይ በሆስፒታሉ የታካሚዎች መጨናነቅን እና አላስፈላጊ መዘግየትን ማስከተሉን ገልፀዋል፡፡

33. በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ መሠረት ተመላላሽ ታካሚዎችን በማንኛውም መደበኛ የስራ ስዓት ለመቀበል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ እየተተገበረ መሆኑን ይህም የታካሚዎችን ቅሬታና መጨናነቅን እንዲሁም አላስፈላጊ መዘግየትን እንደቀነሰ ለበላይ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጅ በሁለቱም ሆስፒታሎች የሪፈራል ስርዓት ባለመኖሩ ሪፈር ያልተደረጉ ታካሚዎችን ሆስፒታሎቹ የሚቀበሉ መሆኑን፣ ሆስፒታሎቹ በታካሚዎች የተጨናነቁ መሆኑን እና የአገልግሎት መዘግየት መኖሩን የኦዲት ቡድኑ በሁለቱ ሆስፒታሎች በአካል ተገኝቶ ባደረገው ምልከታ እና ታካሚዎችን በመጠየቅ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

34. ኦዲቱ የተከናወነባቸው አራቱ ሪፈራል ሆስፒታሎች የዶክተሮች የጠዋት ስብሰባን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጠዋት ስብሰባ የሰዓት ገደብ አለመኖሩ ለታካሚዎች የቆይታ ጊዜ መራዘም ምክንያት መሆኑ ስለታመነበት ሆስፒታሎች የጠዋት ስብሰባ ሰዓት በመወሰንና ለታካሚዎች ሥራ የሚጀምሩበትን ሰዓት በማሳወቅ ችግሩን ለመፍታት እየሞከሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

35. ይህ በመሆኑ በታካሚዎች ላይ አላስፈላጊ መዘግየትን፣ በሆስፒታሎቹ የታካሚዎች መጨናነቅን እና ታካሚዎች ላይ ተጨማሪ ወጪ ያስከተለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በምልክቶችና በቀለም መለየታቸውን በተመለከተ

36.የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ፣ የተኝቶ ህክምና እና የድንገተኛ ህክምና ክፍሎችን በቀላሉ ለመለየት በሚያስችሉ ምልክቶች እና ላልተማረ የህብረተሰብ ክፍል በቀለም ለምሳሌ /ሰማያዊ ለተመላላሽ ታካሚ ክፍል፣ ቀይ ለድንገተኛ ታካሚ ክፍል ወዘተ/ በመቀባት ሊለዩ ይገባል ፡፡

37.በኦዲት በታዩት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የህክምና ክፍሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ምልክቶች በአግባቡ ያልተቀመጡና ምንም አይነት በቀለም የተለየ ክፍል ያለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

38.በኦዲቱ ወቅት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ከሰጡት መልስ እና ከቅሬታ ሪፖርቶች እንደተመለከትነው በሆስፒታሎቹ ምልክቶች ባግባቡ ባለመቀመጣቸው እና ምንም አይነት በቀለም የተለዩ ክፍሎች ባለመኖራቸው በሆስፒታል ግቢው ውስጥ ክፍሎችን በቀላሉ ማግኘት የማይቻል መሆኑንና ታካሚዎች ክፍሎችን በመፈለግ እንደሚጉላሉ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በአካል ተገኝተን ምልከታ ባደረግንበት ወቅት በተለይ በጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በህንፃዎቹ ውስብስብነትና ትልቅነት ምክንያት እንዲሁም በጅማ ዩኒቨርስቲ የሆስፒታሉ ህንፃዎች በሌሎች የዩኒቨርስቲው ህንፃዎች የተከበቡ በመሆኑ በቀላሉ ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን የሚመራና የሚከታተል የሆስፒታል ቦርድ በሁሉም ሆስፒታሎች መቋቋሙን በተመለከተ፤

39. የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥን በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የተጠናከረ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡

40. የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለ ጉዳዩ የሆስፒታሉ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቦርዱ እስካሁን ድረስ

ያልተቋቋመው በዩኒቨርስቲው ባለው የኃላፊዎች ለውጥና አዲስ አሠራር እየተቀረፀ ስለነበር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ቦርድ አለመቋቋሙ በሆስፒታሉ ብዙ ችግሮችን ፈጥሯል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ሆስፒታሉ የውስጥ ገቢውን በቦርድ አስፈቅዶ መጠቀም አለመቻሉ፣ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሊተገበር ያለመቻሉ፣ ሆስፒታሉ የራሱን እስትራቴጂክ እና አመታዊ እቅድ ማዘጋጀትና ማፀደቅ አለመቻሉ እንዲሁም የሥራ ክንውኑን መከታተል እንዳይቻል አድርጓል፡፡

42. በተመሣሣይ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ማዲካል ኮሌጅ የራሱ የሆነ የአስተዳደር ቦርድ ያልተቋቋመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም ሆስፒታሉ አመታዊ እና እስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቶ በጤና ጥበቃ ስር የሚተዳደሩ ሌሎች የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎችን ብቻ ለሚከታተለው የፌዴራል ሆስፒታሎች ቦርድ ስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የሚያቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህን በተመለከተ የሆስፒታሉ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ማዲካል ኮሌጅ በጤና ጥበቃ ሚ/ር ስር ከሚገኙ ሌሎች ሆስፒታሎች የተለየ አገልግሎት (ማስተማር እና ማከም) የሚሰጥ በመሆኑ የራሱ የሆነ ቦርድ እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል፡፡

43. በሌላ በኩል ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በ2003 ዓ.ም ቦርድ ያቋቋመ መሆኑን፣ ቦርዱም በሰው ኃይል ፍላጎት ጥናትና በጤና አጠባበቅ ድጎማ (health care financing) አተገባበር ዙሪያ እየሠራ እንደሚገኝ አረጋግጧል፡፡ ሆስፒታሉ ስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም በሆስፒታሉ እና በዩኒቨርስቲው መካከል በቅንጅት ተናቦ የመስራት እና የማቀድ ችግሮች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

44. ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል በግንቦት 2003 ዓ.ም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተዘጋጀው የሆስፒታሎች የማሻሻያ ትግበራ መመሪያ (Hospital Reform Implemntation Guideline) መሠረት የአስተዳደር ቦርድ ያቋቋመ መሆኑን፣ ቦርዱ የጤና መድን ሽፋን አተገባበርን እና የህክምና ቱሪዝምን ለመተግበር በመስራት ላይ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሆስፒታሉ ስትራቴጂክ እና

አመታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጅ መሆኑን፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ለቦርዱ እና ለኦሮሚያ ጤና ቢሮ የሚያቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣

45.የትምህርት ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስራቸው የሚገኙ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡትን የህክምና አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩ መስጠታቸውን እንዲሁም አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም መኖሩን በቅንጅት ሊከታተሉ ይገባል፡፡

46.የቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መደበኛ ክትትልና ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መደበኛ ባይሆንም አልፎ አልፎ ክትትል እና ድጋፍ የሚያገኝ ቢሆንም ከትምህርት ሚኒስቴር ግን የቴክኒክ ድጋፍም ሆነ ክትትል የማያገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ የጎንደርና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ሆነ ከትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ ክትትል አለማግኘታቸው ታውቋል፡፡

47.የጅማና የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ተጠሪነታቸው ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሲሆን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል እና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተጠሪነታቸው ሆስፒታሉ ለዩኒቨርስቲው ፕሬዘዳንት እንዲሁም ኮሌጁ ለምክትል ፕሬዘዳንቱ ሲሆን የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ ከትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መደበኛ ክትትልና ድጋፍ አለመኖሩ ታዉቋል፡፡

48.የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችንና የህክምና መገልገያ ቁሣቁሶችን አቅርቦትና አጠቃቀም በመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ እና በመድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አማካኝነት ክትትል የሚያደርግ ሲሆን የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ የጅማና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች በዚህ ዙሪያ

ከየትኛውም አካል መደበኛ የሆነ ክትትልና ድጋፍ እንደማይደረግላቸው በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

49.ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ በየትኛውም አካል በባለቤትነት አለመያዙ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል የሚመጡ ድጋፎችን በመደበኛነት አለማግኘታቸው፣ የመድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች እጥረት፣ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መሳሪያዎች ሳይወገዱ ለብዙ ጊዜ በመጋዘን ውስጥ የመከማቸት ችግሮች መኖራቸው ታዉቋል፡፡

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የላቦራቶሪ ግብዓቶችን እና መመሪያዎችን በተመለከተ፤

50.የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ላቦራቶሪዎች ምቹ የሥራ ቦታ እና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ('ሪኤጀንት'፣ 'አናላይዘር'፣ 'ኮንስዩሜብልስ' ወዘተ) ሊኖራቸው፤ የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝ እና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ ሊኖራቸው፤ እንዲሁም የላቦራቶሪ ክፍል የምርመራ ውጤት እንደደረሰ ለታካሚዎች ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

51.የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ የተለየ መመሪያ የሌለው መሆኑ፣ በቂ የላቡራቶሪ ክፍል፣ ናሙና መቀበያ ቦታ እና የግብአት አቅርቦት ችግር መኖራቸውን እንዲሁም የ'ኬሚስትሪ ባክአፕ' እና 'ዩፒኤስ' እጥረት መኖሩ ታውቋል፡፡

52.ስለ ጉዳዩ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተቀላጠፈ የግዥ አሠራር ሂደት ባለመኖሩ የ'ሪኤጀንት' አቅርቦት ችግር መኖሩን፣ በሪኤጀንት እጥረት ምክንያት ናሙናዎች በሆስፒታሉ የማይሰሩ መሆኑ እና ታካሚዎች ወደ ግል ላብራቶሪ የሚሄዱበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም በሆስፒታሉ አንድ 24 ሰዓት ያለማቋረጥ የሚሠራ የኬሚስትሪ ማሽን ያለው ሲሆን ማሽኑ 24 ሰዓት ያለማቋረጥ በመስራቱ በየጊዜው የሚበላሽ መሆኑ፣ በቂ 'ዩፒኤስ' ባለመኖሩ የኤሌክትሪክ ኃይል በሚቋረጥበት ጊዜ በማሽኑ የገባው ናሙና እንደ አዲስ እንዲጀመር እና ተጨማሪ ሪኤጀንት በመጠቀም ለብክነት የሚያጋልጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

53.በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የላቦራቶሪ ጥራት መመሪያ፣ የላቦራቶሪ ባዮ ሴፍቲ መመሪያ እና ለማህበረሰብ የጤና ላቦራቶሪዎች የጤና እና ደህንነት መመሪያዎች ቢኖሩም በመመሪያው መሰረት ሙሉ በሙሉ እንዳልተተገበሩ በኦዲቱ ወቅት የላቦራቶሪ ኃላፊዎችን በመጠየቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሆስፒታሉ የላቦራቶሪ ግብዓት እጥረት (reagent, hormone analyzer)፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እጥረትና በቂ ቦታ ባለመኖሩ የካንሰር ምርመራ መስራት እንዳልቻለ ታውቋል፡፡

54.በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላብራቶሪ ናሙና አሰባሰብን በተመለከተ ፖሊሲ እና መመሪያ ቢኖርም የሆስፒታሉ ላብራቶሪ የሪኤጀንት እና ማቅለጫዎች አቅርቦት ችግር፣ የላብራቶሪ ቁሣቁሶች እጥረት፣ የናሙና መጓጓዣ ችግር፣ የናሙና መሰብሰቢያ ቅፅ ላይ ሙሉ የሆነ የታካሚ መረጃ ያለመሙላት፣ የናሙና እና የውጤት አያያዝ ችግሮች ማለትም ያለቦታ የማስቀመጥ፣ ቦታውን መቀየር እና የናሙና ውጤት መጥፋት ችግሮች እንዳሉ ለሆስፒታሉ የላቦራቶሪ ክፍል ኃላፊ በቀረበ መጠይቅ እና ከቅሬታ ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

55.ባጠቃላይ የላቦራቶሪ መመሪያዎች ባለመቀረፃቸው እና የተቀረፁትም ሙሉ ለሙሉ ባለመተግበራቸው፣ የተሟላ የግዥ ዕቅድ ባለመኖሩ እንዲሁም ለላቡራቶሪ ማሽኖቹ መለዋወጫ እና ሪኤጀንቶች ባለመሟላታቸው የአገልግሎት መቋረጥ ችግር መኖሩ፣ ታካሚዎች ወደ ግል ላቦራቶሪዎች እንዲሄዱ መገደዳቸው እንዲሁም ሆስፒታሎች የላብራቶሪ ውጤት እንደደረሰ የማይሰጡ በመሆኑ ታካሚዎችን ለአላስፈላጊ እንግልት፣ መዘግየት እና ለተጨማሪ ወጭ እንዲሁም የተገልጋዩን ፍላጎት ማሟላት እንዳይቻል ማድረጉ ታውቋል፡፡

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ መሆናቸውን በተመለከተ፤

56. በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጡ ትምህርት እና ስልጠናዎች የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን የማይጎዱ ሊሆኑ እና ሆስፒታሎች የህክምና ዶክተሮችን በስራ ስዓት ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

57.በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል እና በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል የህክምና እና የማስተማር አገልግሎት ላይ የትኛው ቅድሚያ ማግኘት አለበት በሚለው ዙሪያ ግልፅ የሆነ አሰራር አለመኖር ይህም በህክምና ዶክተሮች መሀከል እያከሙ ማስተማር (ለህክምና አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት) ወይንም እያስተማሩ ማከም (ለትምህርትና ስልጠናዎች ቅድሚያ መስጠት) የሚል ግልፅ የሆነ የግንዛቤ እጥረቶች መኖራቸው፤ ይህንንም ለመወሰን የተዘጋጀ ግልፅና ወጥ መመሪያ ያለመኖሩ፤ እንዲሁም ሃኪሞች የስራ ሰዓታቸውን ለሆስፒታሉ አገልግሎት ብቻ የሚያውሉ መሆኑን የሚከታተሉበትና የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

58. ይህንንም በተመለከተ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ እስካሁን ባለው አሰራር መሰረት 85% ለማስተማር እና 15% ለህክምና የሚያውሉ መሆኑን ለዚህም ግልፅ የሆነ መመሪያ ያለመኖሩን፣ በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሐኪሞች 70% ሰዓታቸውን በማከም 30% ደግሞ በማስተማር እና ምርምር ስራ ላይ እንዲያውሉ የተጠና ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ትግበራ አለመጀመሩን፣ ሐኪሞችን በስራ ስዓት ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ እና አሰራር አለመኖሩን፣ ይህም የህክምና ባለሞያዎች እጥረት በመኖሩ ለቀው ወደሌላ የግል ህክምና ተቋማት ይሄዳሉ ከሚል ስጋት የመጣ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59.የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ለህክምና አሰጣጥና እና ለትምህርት የተመደበ ስዓትን በተመለከተ የኮሌጁ ሕግ 40% ለህክምና አገልግሎት፣ 40% ለትምህርት እና 20% ለምርምር ሥራ እንዲውል ይገልፃል፡፡ ሆኖም የኦዲት ቡድኑ ከሆስፒታሉ የሐኪሞች የሰዓት አጠቃቀምን የሚገልፅ መረጃ አላገኘም፡፡ እንዲሁም ሐኪሞችን በስራ ስዓት ለመከታተል የሚያስችል ዘዴ እና አሰራር አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

60.የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በሕክምና አገልግሎት እና የትምህርት ስዓት አከፋፈል መካከል ግልፅ የሆነ መመሪያ አለመኖሩን፣ ሆስፒታሉና የሕክምና ኮሌጁ ራሳቸውን የቻሉ የዩኒቨርስቲው የሥራ ሂደቶች

በመሆናቸው በቅንጅት እቅዶችን እንደማያዘጋጁ፤ የሕክምና እና ትምህርት አገልግሎት በምን መልኩ ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት ስምምነት ላይ መድረስ አለመቻላቸውን እንዲሁም የህክምና ዶክተሮች የትምህርት ሚኒስቴር ቅጥር ስለሆኑ ሆስፒታሉ በስራ ስዓት መከታተል እንደማይችል ገልፀዋል፡፡

61.በጅማ ዩኒቨርስቲ ሪፈራል ሆስፒታል የህክምና አገልግሎት፣ የማስተማርና የምርምር የጊዜ ክፍፍል 40% ለህክምና አገልግሎት፣ 40% ለማስተማር እና 20% ለምርምር ቢሆንም ሆስፒታሉ ለህክምና አገልግሎት የተሰጠውን የሥራ ስዓት ተፈፃሚነት እንደማይከታተል ታውቋል፡፡ የሐኪሞችን የስራ ስዓት መከታተያ ዘዴን በተመለከተ ኃላፊዎቹ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለስፔሻሊስቶች የመቆጣጠሪያ ዘዴ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡

62.ስለ ጉዳዩ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በሰጡት መልስ የጤና ጥበቃ አቅጣጫ ለህክምና አገልግሎት ትኩረት መስጠት በመሆኑ እያከሙ ማስተማር የሚለውን አቅጣጫ የምንሰጥ ቢሆንም በትምህርት ሚኒስቴርና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ወጥ መመሪያ አለመቀመጡን ገልፀዋል፡፡

63.ከተሰበሰቡ የኦዲት ማስረጃዎች እና ከቃለመጠይቆች ለማረጋገጥ እንደተቻለው የተመላላሽ ህክምና ክፍል ሐኪሞች በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከሥራቸው የማይገኙበት፣ ዘግይተው የሚገቡበት እና የመውጫ ስዓት ሳይደርስ ቀድመው የሚወጡባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ፣ በዚህም ምክንያት በታካሚዎች ላይ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ብዙ ስዓት መጠበቅ፣ ለተጨማሪ ወጪ መዳረግ (በተለይ ከገጠርና ከሩቅ ቦታ በሚመጡ ታካሚዎች ላይ) እና መጉላላትን እየፈጠረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በፌደራል ሪፈራል ሆስፒታል የሚታከሙ ተመላላሽ ታካሚዎች በስፔሻሊስት ሀኪም የሚታዩ መሆኑን በተመለከተ፤

64.ተመላላሽ ታካሚዎች በሆስፒታሉ በተመዘገቡበት ዕለት በስፔሻሊስት ሃኪም የህክምና አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል፡፡

65.በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላላሽ ታካሚዎች በጠቅላላ ሀኪም ወይንም በሪዚደንት ሀኪም እንደሚታዩ ታውቋል፡፡ ይህን በተመለከተ ለሆስፒታሉ ኃላፊዎች በቀረበ መጠይቅ በአነስተኛ ደረጃ ባሉ ሆስፒታሎች ሊታከሙ የሚችሉ ተመላላሽ ታካሚዎች ስለሚመጡ በጠቅላላ ሀኪም ወይንም በሪዚደንት ሀኪም እንደሚመረመሩ ይሁን እንጅ የስፔሻሊስት እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በቀጠሮ በስፔሻሊስት ሃኪሞች እንደሚታዩ ገልፀዋል፡፡

66.በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የአእምሮ እና የአይን ታካሚዎች በስፔሻሊስት የሚታዩ ሲሆን ሌሎቹ ግን ስፔሻሊስት አያገኙም፡፡ ሆኖም ግን በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተቀመጠው ሁሉም ተመላላሽ ታካሚዎች ስፔሻሊስት፣ ሪዚደንት ሀኪም፣ ጠቅላላ ሀኪም እና ተማሪ ሀኪምን ባካተተ ቡድን እንደሚመረመሩ ቢገልፅም ከቅሬታ ሪፖርቶች ለመረዳት እንደተቻለው ስፔሻሊስት ሃኪሞች እንደማይገኙ እና የተመደቡት ሃኪሞችም በተሟላ ሁኔታ የማይገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

67.የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች ተመላላሽ ታካሚዎችን ካለ መላኪያ/ሪፈር ወረቀት ስለሚቀበሉ እና የስፔሻሊስት ሀኪሞች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ህሙማኑ በተማሪ ሀኪም እንደሚታዩ በኦዲቱ ወቅት ለሆስፒታሎቹ የበላይ ኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ምላሽ እና ከተከለሱ የኦዲት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

68.ይህም በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች በሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ እና የታካሚዎችን በስፔሻሊስት ሀኪም የመታከም ፍላጎት ማሟላት እንዳልተቻለ ታውቋል፡፡

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና እና የምርመራ መሳሪያዎች መኖራቸውን በተመለከተ፤

69.በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለታካሚዎች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል በቂ የሆነ የህክምና እና የዲያግኖስቲክ መሳሪያዎች ሊኖሩ እንዲሁም የህክምና መሳሪያዎች ከአገልግሎት በፊትና ከአገልግሎት በኋላ መደበኛ የሆነ የፍተሻ እና የጥገና አገልግሎት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

70.በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ‘ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ’ (MRI) ማሽን የሌለ እና የኬሚስትሪ ማሽን እጥረቶች መኖሩ ታውቋል። ይህንንም በተመለከተ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሆስፒታሉ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል ያሉት የሕክምና መሣሪያዎች ከተጠቃሚው ቁጥር አንፃር በቂ ባይሆኑም ዘመናዊ መሳሪያዎች እንዳሉት፣ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች የጥገና ችግር መኖሩን፣ በሆስፒታሉ የህክምና መሳሪያዎች ጥገና ክፍል (bio-medical engineering department) የተቋቋመ ቢሆንም የሚሰጠው አገልግሎት ከሆስፒታሉ ፍላጎት አንፃር በቂ ያለመሆኑ እና የቅድመ መከላከል ፍተሻ አገልግሎት እንደማይሰጥ፣ የአንዳንድ መሳሪያዎች ግዥ ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚፈፀም በመሆኑ የጥገናውንም አገልግሎት የሚሰጠው አቅራቢው ብቻ በመሆኑ ሙሉ የጥገና አገልግሎት ለማግኘት የሚዘገይ መሆኑን ገልፀዋል።

71. በተመሣሣይ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል በቂ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች የሌሉት መሆኑን፣ የላብራቶሪ ማሽኖች ለምሳሌ ሆርሞን አናላይዘር፣ ቫይራል ሎድ፣ ፋክስ ካሊበር፣ 5DF፤ ሄማቶሎጂ እና የምርመራ መሣሪያዎች እንደ ‘ሲቲስካን’ (CT-Scan) የተከላ ስራው ቢጀመርም ያልተጠናቀቀ መሆኑን፤ ‘ማግኔቲክ ሪዞናንት ኢሜጅንግ’ (MRI) በከፍተኛ ወጪ ግዥ ቢፈፀምም የማሽኑ ማስቀመጫ ቦታ ግንባታ ባለመጠናቀቁ ምክንያት እስከአሁን ያልተተከለ መሆኑን፣ ማሞግራፍ፣ ቫስኩላር አልትራሳውንድ በቦታ እጥረት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑን፤ ‘ኤሌክትሮካርዲዮግራም’ (ECG) እና ‘ኢኮካርዲዮግራም’ (ECO-Cardiogram) መሳሪያዎች በተመላላሽ ህክምና ክፍል የሌሉት መሆኑን፤ በተጨማሪም አሁን ሆስፒታሉ እየተጠቀመበት ያለው የአልትራሳውንድ ማሽን ከአሥር ዓመት በፊት ጀምሮ ያለ ሲሆን በራጅ ክፍል የራጅ ወረቀት ማድረቂያው በቂ ባለመሆኑ ፊልሙን ለማንበብ ብዙ ስዓት እንደሚፈጅ ለባለሙያዎች ከቀረበ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል።

72. በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ለህክምናና የምርመራ መሣሪያዎች ከአገልግሎት በፊት ፍተሻ የሚደረገው በሆስፒታሉ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ፣ ከዚህም ውስጥ የላቦራቶሪ መሳሪያዎችን በላብራቶሪ ባለሙያዎች አማካኝነት ሲሆን ከአገልግሎት በኋላ ግን በዚህ ዙሪያ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ስለሌሉ በቂ ጥገና አይደረግላቸውም፡፡ ሆኖም የመሣሪያዎች ብልሽት ካጋጠመ ሆስፒታሉ መሣሪያዎችን ወደ ኢትዮጵያ የጤና እና የሥነ-ምግብ ምርምር ተቋም (Ethiopian Health & Nutrition Research Institute) ወስዶ እንደሚያሰራ /እንደሚያስጠግን/ ይህም ብዙ ጊዜ በሚወስድበት ወቅት የሆስፒታሉን አገልግሎት አሰጣጥ ሊያዘገይ እንደሚችል ታውቋል፡፡ በኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ አንድ የኬሚስትሪ ማሽን እና አንድ ሄማቶሎጂ ማሽን ከአገልግሎት በኋላ ጥገና ባለማግኘታቸው ምክንያት ከሥራ ውጭ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡

73. በጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል የሕክምና መሣሪያዎች ከተጠቃሚዎች ብዛት አንፃር ሲታይ በቂ አለመሆኑ እና ሆስፒታሉ ለህክምና መሣሪያዎች የጥገና አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል በ2004 ዓ.ም ያቋቋመ ቢሆንም ከ2004 በፊት በበቂ ሁኔታ ጥገናዎች እየተከናወኑ እንዳልነበር ለሆስፒታሉ የበላይ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

74. በተመሳሳይ በጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆሰፒታል የሕክምና እና የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ከተጠቃሚዎቹ አንፃር ሲታይ በቂና ዘመናዊ አለመሆናቸው ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሆስፒታሉ የጥገና ክፍል እንደሌለው ተረጋግጧል፡፡ የሆስፒታሉ ላውንደሪ ማሽንም ባለመጠገኑ ምክንያት እስከ ግንቦት 2004 እየሠራ እንዳልነበር ታውቋል፡፡ ስለ ጉዳዩ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግሩን ለማቃለል /ለመፍታት/ ሆስፒታሉ ከአገልግሎት በኋላ ከኢትዮጵያ የጤና እና ሥነ-ምግብ ምርምር ተቋም ጥገና ለማግኘት እየሞከሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

75. በዚህ ምክንያት በቀላሉ ሊጠገኑ የሚችሉ የህክምና መሣሪያዎች ከአገልግሎት በኋላ ጥገና ስለማይደረግላቸው ለብዙ ጊዜ ከሥራ ውጭ ሆነው መቀመጥ፣ የአገልግሎት መቆራረጥና ዝቅተኛ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት የመስጠት፣ ታካሚዎችን ወደ ግል ክሊኒክና ሆስፒታሎች በመላክ ለተጨማሪ ወጪ፣ ለአላስፈላጊ መዘግየት

እና የታካሚዎችን ፍላጎት አለማርካት፣ ለአብዛኞቹ የህክምና መሣሪያዎች ጥገና የሚደረገው በውጭ ባለሙያዎች በመሆኑ በሆስፒታሎች ላይ ተጨማሪ ወጪና የጊዜ ብክነትን አስከትሏል፡፡

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ በቂ የሆነ የታካሚዎች ማረፊያ ቦታ፣ መፀዳጃ ቤት፣ 24 ሰዓት የውሃና የመብራት አገልግሎት እና የኢንፌክሽን መከላከል ክፍል መኖሩን በተመለከተ፤

76.በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ በቂ የመጸዳጃ ቤት፣ የታካሚዎች ማረፊያና የበሽታ መከላከያ (infection prevention) አገልግሎቶች እንዲሁም 24 ሰዓት የውሃ እና የመብራት አገልግሎት ሊኖሩት ይገባል፡፡

77.በጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያለ እና ክፍሉም በኢንፌክሽን መከላከያ መመሪያ መሰረት ደረቅና ፍሣሽ ቆሻሻዎችን የተለያየ ቀለም ባላቸው ቅርጫቶች በማዘጋጀት ቆሻሻዎችን የማስወገድ ሥራዎች እየተሠሩ ቢሆንም በሆስፒታሉ የተመላላሽ ታካሚዎችን ቁጥር ያገናዘበ የመፀዳጃ ቤት የሌለ መሆኑን፣ ለታካሚዎች በቂ የማረፊያ ቦታ የሌለ መሆኑን፣ በሆስፒታሉ የስትሬቸር እጥረት መኖሩን፣ የውሃ አቅርቦት ችግር በመኖሩ ከ6ኛ-8ኛ ፎቅ ውሃ የማይደርስ መሆኑ ታውቋል፡፡

78.ይህን በተመለከተ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የተመላላሽ ታካሚዎች የመፀዳጃ ቤት ብዛት አናሳ ቢሆንም በአጠቃቀም ችግር ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ የሚሆኑ መሆኑን፣ በሆስፒታሉ በቂ ስትሬቸር ቢኖርም ስትሬቸሩ ላልተፈለገ አላማ እየዋለ በመሆኑ መጋዘን ውስጥ እንዲቆለፍበት ውሣኔ ማሳለፋቸውን፣ በሆስፒታሉ ስር የሰደደ የውሃ ችግር ያለ መሆኑን ይህም ሆስፒታሉ ሲሰራ የውሃ መስመሮቹ ኮፐር በመሆናቸው ለጥገና እና ላላስፈላጊ ወጪ መዳረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

79. የኦዲት ቡድኑ በኦዲቱ ወቅት እንደተመለከተው በቂ ቦታዎች፣ የመቀመጫ ወንበሮች እና ሌሎች አገልግሎቶች ባለመኖራቸው ታካሚዎች ብዙ ጊዜያቸውን ቆመው፣ በጊቢውና በየኮሪደሩ ተኝተውና ተቀምጠው እንዲጠብቁ መገደዳቸውን፣ ስትሬቸር ባለመኖሩ ምክንያት የተጎዱ ሰዎች በሰዎች ሸክም ወደ ሆስፒታሉ

እንደሚገቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የሆስፒታሉ አስተዳደር የመፀዳጃ ቤቶችን እና የውሃ እጥረትን በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ባለመሞከሩ ችግሮቹ እየተባባሱ መምጣታቸውን አረጋግጧል፡፡

80. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያለውና ክፍሉም በኢንፌክሽን መከላከያ መመሪያ መሰረት ደረቅና ፍሣሽ ቆሻሻዎችን የተለያየ ቀለም ያላቸው ቅርጫቶች በማዘጋጀት ቆሻሻዎችን የሚያስወግድ ቢሆንም በሆስፒታሉ ከፍተኛ የመፀዳጃ ቤት ችግር መኖሩ ታውቋል፡፡

81. የጅማና የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች የኢንፌክሽን መከላከያ ክፍል ያልተቋቋመ እንዲሁም የኤሌክትሪክ መቆራረጥ እና በቂ የመፀዳጃ ቤቶች አለመኖራቸው ታውቋል፡፡ ይህንን በተመለከተ የስራ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የኢንፌክሽን መከላከያ ኮሚቴ /ክፍል/ ያልተቋቋመ መሆኑን እንዲሁም የሆስፒታሉ መፀዳጃ ቤቶች ቁጥር ከሚፈለገው በታች መሆኑንና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚቆራረጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የመድኃኒት አቅርቦት እና አጠቃቀምን የሚከታተል የመድሃኒት እና ቴራፔቲክ ኮሚቴ (Drug and Therapeutic Committee) መቋቋሙን በተመለከተ፤

82.የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶችን ዝርዝር የሚያዘጋጅ፣ የመድሃኒት አያያዝ ስርዓት የሚከታተል እና የመድኃኒቶችን ግዥ አቅርቦትና አጠቃቀም የሚከታተል ኮሚቴ (DTC) ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡

83.የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የመድኃኒትና ቴራፔቲክ ኮሚቴ በ2003 ዓ.ም ቢያቋቁሙም በሙሉ አቅሙ እየሰራ እንዳልሆነ እንዲሁም በሆስፒታሉ ፋርማሲዎች በቂና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች አቅርቦት ችግር መኖሩ ታውቋል፡፡

84. ስለ ጉዳዩ የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ኮሚቴውን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ገልፀው በመድሃኒቶች አቅርቦት ዙሪያ ከግዥ እቅድ ጀምሮ ችግሮች መኖራቸው ይህም ከሆስፒታሉ አደረጃጀት ጋር ሊቀረፍ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

85.በተመሣሣይ መልኩ በቅዱስ ጳውሎስ፣ በጅማና ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች በ2003 መጨረሻ አካባቢ ኮሚቴው የተቋቋመ ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በአግባቡ እንዳልተደራጀ ታውቋል፡፡ ይህን በተመለከተ የሆስፒታሎቹ የበላይ ኃላፊዎች እንደገለፁት አንዳንድ ችግሮች ለምሳሌ አስፈላጊ በሆኑ መድኃኒቶች አቅርቦት እና ክትትል፣ አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችን ዝርዝር አለማዘጋጀት፣ ከህክምና መሣሪያዎችና መድኃኒት አቅራቢዎች ጋር ያለመናበብና ምቹ የሆነ የሥራ ግንኙነት አለመፍጠር እና አስፈላጊ መድኃኒቶችን በሚያስፈልግ ደረጃ ያለመያዝ ችግሮች መኖራቸውን እና ችግሮቹ አሁንም ያልተቀረፉ እና የመድኃኒትና ቴራፒዩትክ ኮሚቴ ድጋፍ የሚጠብቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

86.የሆስፒታሉ ፋርማሲዎች አስፈላጊ መድሃኒቶችን በበቂ ሁኔታ ባለመያዛቸው ምክንያት ታካሚዎች ወደ ግል ፋርማሲዎች ስለሚላኩ ለተጨማሪ ወጪ፣ ለአላስፈላጊ መዘግየት እና የታካሚዎችን ፍላጎት ያለማሟላት ችግሮች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ተገንዝቧል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

87.በፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች (ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል) ለተመላላሽ ታካሚዎች ቀልጣፋ እና ውጤታማ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ የዚህ ክዋኔ ኦዲት ዓላማ የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ትምህርት ሚኒስቴር) ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋታቸውን ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ ዓላማ አንፃር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡ እና የክትትል ስርዓቱ አፈፃፀም ውጤታማነት በተመለከተ የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል።

88.የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለሁሉም ፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሆን ወጥ የሆነ የህሙማን አላላክና አቀባበል/ሪፈራል/ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ አለመውጣቱ፤

89.ጥቁር አንበሳና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልዎች ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ሠዓት የማይቀበሉ መሆኑ፤

90.በአራቱም የፌዴራል ሪፌራል ሆስፒታሎች የሐኪሞች የጠዋት ስብሰባ የጊዜ ገደብ አለመኖሩ፤

91.በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ግቢ ውስጥ ክፍሎችን ለማመላከት የሚያስችሉ ምልክቶች እና ቀለሞች አለመኖራቸው፣

92.በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የአስተዳደር ቦርድ አለመቋቋሙ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ ለፌደራል ሆስፒታሎች ቦርድ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ቢያቀርብም ከሚሰጠው አገልግሎት አኳያ (ማስተማርና ማከም) የራሱ የሆነ የአስተዳደር ቦርድ አለመኖሩ፤

93.በትምህርት ሚኒስቴር ስር ባሉ የዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም በመደበኛነት የሚከታተል እና ድጋፍ የሚያደርግ አካል አለመኖሩ፣

94.በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ የሚገልፅ መመሪያ አለመኖሩ፤

95.በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የላብራቶሪ ግብአቶች እና መሣሪያዎች እጥረት መኖሩ፤

96.በአራቱም ፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ውስጥ የህክምና አገልግሎት እና የትምህርት /ስልጠና ጊዜን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ እና አፈፃፀም አለመኖሩ፣ ሐኪሞችን በሥራ ሰዓት ስለመገኘታቸው ክትትል የማይደረግ መሆኑ፤

97.በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና እና የምርመራ መሣሪያዎች አለመኖራቸው፤

98.በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች መፀዳጃ ቤቶች በቂ አለመሆን፣ በተደጋጋሚ የውሃና የመብራት ኃይል መቆራረጥ፣ በቂ የመጠበቂያ ቦታ እና ስትሬቸር አለመኖሩ፤

99.በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚገኙ የመድኃኒትና ቴራኘዩትክ ኮሚቴዎች አለመጠናከራቸው፤

በአጠቃላይ የፌደራል ሪፈራል ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ እና የተገልጋዩን ፍላጎት የሚያረካ እንዳይሆን እንዳደረገው የኦዲት ቡድኑ ተገንዝቧል፡፡ ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የታካሚዎችን አቀባበል እና የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና የታካሚዎችን ፍላጎት የሚያሟላ እንዲሆን ለማስቻል፤

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንደየሆስፒታሎቹ ስፔሻላይዜሽን ሁሉንም ሆስፒታሎች ማለትም ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ከፍተኛ (ሶስተኛ) ደረጃ ያሉትን ሆስፒታሎች በመረጃ መረብ በማገናኘት አገር አቀፍ የህሙማን አላላክና አቀባበል/ሪፈራል ስርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም በሆስፒታሎች መካከል የእርስ በርስ የስራ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና ባለሙያዎች ለታካሚዎች/ለተገልጋዩ የሚሰጡት አገልግሎት እንዲጨምር እና የህክምና ባለሙያዎቹ በስራቸው ዙሪያ የህግ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል በአገር አቀፍ ደረጃ ታካሚዎችን መሰረት ያደረገ የህክምና ሥነ- ምግባር መመሪያ (ethical and medico-legal regulation) ሊያወጣ ይገባል፡፡
- የተመላላሽ ታካሚዎችን አቀባበል ለማቀላጠፍ እና የሆስፒታል ቆይታ ጊዜ ለመቀነስ ሆስፒታሎች የተመላላሽ ታካሚዎችን በማንኛውም የሥራ ሰዓት ሊቀበሉ እና የተመላላሽ ታካሚዎች የመጀመሪያ የህክምና አገልግሎት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በተቀመጠው መሰረት በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሊያገኙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሕክምና ዶክተሮች ለጠዋት የስብሰባ ጊዜያቸው የሰዓት ገደብ ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡
- አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተደራጀ የሆስፒታል እቅድ ለመስራት፣ የሂሳብ ቁጥጥር ለማድረግ፣ የሆስፒታሉ ንብረቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ እና አጠቃላይ የሆስፒታሉን የስራ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር/ለመከታተል፣ በጀት እና የዕቅድ አፈፃፀም

ሪፖርቶችን ገምግሞ በማቅረብ የሚያስፀድቅ እንዲሁም በፀደቀው መሠረት መተግበሩን የሚከታተል የሆስፒታል አስተዳደር ቦርድ ሊያቋቁሙ ይገባል፡፡

- በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የተመላላሽ፣ የድንገተኛ እና የተኝቶ ህክምና ክፍሎች በቀላሉ ለማግኘት እንዲቻል ለታካሚው በግልፅ ሊታዩ በሚችል መልኩ ምልክቶች ሊቀመጡ እና ላልተማረ የህብረተሰብ ክፍል እንዲያመላክቱ ክፍሎቹ በቀለም ሊለዩ ይገባል፡፡
- በዩኒቨርስቲ ሆስፒታሎች አስፈላጊ መድሃኒቶችን እና የህክምና መሳሪያዎችን አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሁም አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚከታተል እና ድጋፍ የሚያደርግ ክፍል በትምህርት ሚኒስቴር ስር ሊቋቋም፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህክምና አገልግሎት አሰጣጡን እና የማስተማርና የምርምር ስራውን በቅንጅት እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት (memorandum of understanding) ሊኖር ይገባል፡፡
- አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሰው ኃይላቸውንና በጀታቸውን በአግባቡ ለመጠቀም፣ የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ እቃዎች/ግብዓቶች፣ መድሀኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች በሚፈለገው መጠን ለማግኘት እንዲያስችላቸው የስትራቴጂክ ዕቅድና ዓመታዊ ዕቅድ ሊያዘጋጁ እንዲሁም ባወጡት ዕቅድ መሠረት የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
- የጥቁር አንበሣ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላቦራቶሪ ናሙና አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ እና በመመሪያው መሰረት ሊሰራ እንዲሁም ሆስፒታሉ ምቹ የላቦራቶሪ አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ የኬሚስትሪ ማሽንና ባክ-አፕ (Back Up) ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም ጅማ ዩኒቨርስቲ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የላብራቶሪ ሪኤጀንትና አናላይዘርስ አቅርቦት ችግርን፣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እጥረትን፣ የላብራቶሪ ውጤት መጥፋትና የታካሚን ሙሉ መረጃ ያለመሙላት ችግሮችን በመለየት መፍትሔ ሊሰጡ ይገባል፡፡

- አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የትምህርት /ሥልጠና ጊዜ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥን በማይጎዳ መልኩ ሊያስኬዱ እና የሀኪሞችን የስዓት ክፍፍል ለይተው ሊያስቀምጡ፣ እንዲሁም በሪፖርት፣ በሳምንታዊ እቅድና ክንውን፣ በትምህርት ክፍል ኃላፊዎች አማካኝነት ወዘተ የህክምና ዶክተሮችን በስራ ስዓት ሊከታተሉ ይገባል፡፡

- በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩት አራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች እንደ ሦስተኛ ደረጃ ሆስፒታል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ጥራት ያለውና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዘመናዊና በቂ የሆነ የህክምና ምርመራ መሣሪያዎች ሊኖራቸው እንዲሁም መሳሪያዎቹ መደበኛ የቅድመ ምርመራ ፍተሻ እና ከአገልግሎት በኋላ ጥገና ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

- የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች እንደታካሚው ብዛት ተመጣጣኝ መፀዳጃ ቤቶች ሊኖራቸው፣ በተደጋጋሚ የውሃና የመብራት መቆራረጥ ችግሮችን እንደየአስፈላጊነቱ ተለዋጭ/ተጠባባቂ አገልግሎቶችን በመጠቀም መፍትሔ ሊበጅ፣ በቂ የሆነ የታካሚዎች ማረፊያ ቦታ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- በአራቱም የፌዴራል ሪፈራል ሆስፒታሎች የሚገኙት የመድኃኒትና ቴራኘዩትክ ኮሚቴዎች (DTCs) የአስፈላጊ (essential) መድኃኒቶችን ዝርዝር ዝግጅት፣ አቅርቦት፣ ግዥ፣ አጠቃቀምና ቁጥጥር በሚገባ ሊፈፅሙ በሚችሉ መልኩ ሊጠናከሩ ይገባል፡፡